ከናንተ በፊት ከነበሩት ህዝቦች መካከል አንድ የቆሰለ ሰውዬ ነበር። ትእግስት በማጣቱም ቢላ አንስቶ እጁን ቆረጠ። እስኪሞት ድረስም ደሙ አልተቋረጠም። አላህም እንዲህ አለ: 'ባሪያዬ ነፍሱን በማውጣት ተቻኮለኝ። በርሱ ላይም ጀነትን እርም አድርጌበታለሁ።'

ከሐሰን እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ጁንዱብ ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እዚሁ መስጂድ ውስጥ ነገሩን። ከነገሩን ጀምሮም አልረሳነውም። ጁንዱብም በአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ
ይስፈን) ላይ ዋሽቷል ብለንም በፍፁም አንፈራም። እንዲህም አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል: "ከናንተ በፊት ከነበሩት ህዝቦች መካከል አንድ የቆሰለ ሰውዬ ነበር። ትእግስት በማጣቱም ቢላ አንስቶ እጁን
ቆረጠ። እስኪሞት ድረስም ደሙ አልተቋረጠም። አላህም እንዲህ አለ: 'ባሪያዬ ነፍሱን በማውጣት ተቻኮለኝ። በርሱ ላይም ጀነትን እርም አድርጌበታለሁ።' "
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ከኛ በፊት ከነበሩት ህዝቦች መካከል መቁሰል ያጋጠመው አንድ ሰውዬ እንደነበር፤ በህመሙ ባለመታገስም ቢላ ይዞ እጁን በመቁረጥ ለመሞት እንደተቻኮለ፤ ደሙም እስኪሞት ድረስ አለመቋረጡን፤ አላህም "ባሪያዬ ነፍሱን በማውጣት ተቻኮለ። በርሱ ላይም ጀነትን እርም አድርጌበታለሁ።" ማለቱን ተናገሩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/2981